የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ-ሰኔ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 44
ADDIS ABABA-24th June, 2004

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፫/፲፱፻፺፮ ዓ.ም
በልማት ወደ ኋላ ለቀሩ ክልሎች ልዩ ድጋፍ
የሚያደርግ የፌደራል ቦርድ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች
ምክር ቤት ደንብ ................................ ገጽ ፪ሺ፮፻፴፬

## CONTENTS

Council of Ministers Regulation No. 103/2004
The Council of Ministers regulation for the Establishment of Federal Board to provide affirmative support for less developed region................. Page 2634

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፫/፲፱፻፺፮**
**በልማት ወደኋላ ለቀሩ ክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ የፌዴራል ቦርድ ማቋቋሚያ**
**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ "ደንብ በልማት ወደኋላ ለቀሩ ክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ የፌዴራል ቦርድ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፫/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ፤

በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩. "በልማት ወደኋላ የቀሩ ክልሎች" ማለት የአፋር ፣ የሶማሌ ፣ የጋምቤላና የቤኒሻንጉል /ጉሙዝ/ ክልሎች ማለት ሲሆን ፤ በኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች ውስጥ የሚገኙትን የአርብቶ አደር አካባቢዎችንም ያካትታል።

፪. "ልዩ ድጋፍ" ማለት በዋነኛነት የዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸምን በሚመለከት የሚደረግ የክልሎቹን ፍላጎት መሠረት ያደረገ እና አቅማቸውን በሚገነባ መንገድ ቀጣይነት ያለው የተቀናጀ እገዛ ነው።

***COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO 103/2004***
***COUNCIL OF MINISTERS REGULATION FOR THE ESTABLISHMENT OF FEDERAL BOARD TO PROVIDE AFFIRMATIVE SUPORT FOR LESS DEVELOPED REGION***

This regulationis is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Demo cratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995.

*1. Short Title*

This regulation may be cited as "The Council of Ministers Regulation for the Establishment of Federal Board to provide affirmative support for less developed regions regulation No. 103/2004

2. *Definitions*

In this Regulation

1) In this Regulations "less developed Regions" means Regional States of Afar, Somali, Gambela and Benshangul Gumuz and shall include pastoral areas in Oromia and Southern Nations Nationalities and People's Regions.
2) "Affirmative support" means sustainable and coordinated support given to the regions mainly with regard to plan preparation and implementation based on their interests.

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unite Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ 1
Negarit G. P.O. Box

፫. <u>መቋቋም</u>

፩/ በልማት ወደኋላ ለቀሩ ክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ ፌዴራል ቦርድ /ከዚህ በኋላ ቦርዱ እየተባለ የሚጠራ/ የሕግ ሰውነት ያለው ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የቦርዱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

፬. <u>ዓላማ</u>

የቦርዱ ዓላማ፤

፩. የፌዴራል መንግሥቱ አካላት በልማት ወደኋላ ለቀሩ ክልሎች የሚሰጡትን ድጋፍ ማቀናጀት፣

፪. ክልሎቹ በራእይና በእቅድ ላይ የተመሰረተ ቀጣይ ልማት የማስፈጸም አቅም ግንባታና የዲሞክራታይዜሽን ሥራ ለማከናወን ለሚያደርጉት ጥረት ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ፡፡

፭. <u>የቦርዱ ኃላፊነትና ተግባር፤</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. የዕቅድ ሃሣብ ያመነጫል፤ በዕቅድ አዘገጃጀትና አፈጻጸም የተቀናጀ ቀጣይ እገዛ ይሰጣል፤

፪. ራሳቸውን የሚያስችል ቀጣይ የአቅም ግንባታ እገዛ ለክልሎቹ ያደርጋል፤

፫. በልማትና በመልካም አስተዳደር ለክልሎቹ የሚደረገውን ሁሉንም የፌዴራል እገዛ ያቀናጃል፤

፮. <u>የቦርዱ አባላት</u>

ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር.................. ሰብሳቢ

፪. የግብርና እና የገጠር ልማት ሚኒስቴር........ አባል

፫. የትምህርት ሚኒስቴር ................................ "

፬. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ................................ "

፭. የውሃ ሀብት ሚኒስቴር ................................ "

፮. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር .................. "

፯. የገቢዎች ሚኒስቴር .................................... "

፰. የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር ........................ "

፯. <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

፩. ቦርዱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫. ቦርዱ ውሣኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሣብ የቦርዱ ውሣኔ ይሆናል፡፡

፬. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፰. <u>የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ኃላፊነትና ተግባር</u>

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ኃላፊነቶችና ተግባሮች ይኖሩታል፤

3. *Establishment*

1) Federal Board to provide affirmative support for less developed regions /herein after referred to as the "Board"/ having its own legal personality is established by these regulations.

2) The Board shall be accountable to the Prime Minister.

4. *Objectives*

The objectives of the board shall be to

1) Coordinate the support given to less developed regions by organs of the Federal Government.

2) Give the necessary support for the regions in their effort to carryout democratization, sustainable development and capacity building based on vision and plan.

5. *Responsibilities and Duties of the Board.*\

The board shall have responsibilities and duties to

1) Initiate planning ideas; give coordinated and sustainable support with respect to plan preparation and implementation.

2) Give sustainable capacity building support to the regions so that they can become self reliant;

3) Coordinate all Federal development and good governance support provided to the regions;

6. *Members of the Board*

The Board shall have the following members:

1) Minister of Federal Affairs................Chairperson

2) Ministry of Agriculture & Rural Development .......................................................... Member

3) Ministry of Education........................ "

4) Ministry of Health............................. "

5) Ministry of Water Resources ............. "

6) Ministry of Trade and Industry ........... "

7) Ministry of Revenues ......................... "

8) Ministry of Development Infrastructure ... "

7. *Meeting of the Board*

1) The Board shall meet once in three months, however, it may meet at any time at the request of the chairperson.

2) There shall be a quorum where more than half of the members are present at a meeting of the Board.

3) Decisions of the Board shall be made by majority vote, and in case of a tie, the chairpersons shall have a casting vote.

4) Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may draw up its own rules of procedure.

8. *Responsibilities and Duties of the Ministry of Federal Affairs.*

The ministry shall have responsibilities and duties to

፩. የቦርዱ ዋና ጽ/ቤትና የፌዴራል እገዛውን የሚያቀናጅ ማእከል ሆኖ ያገለግላል፤ የቦርዱን ውሣኔ አፈጻጸም ይከታተላል፤
፪. የተሻለ አቅም ያላቸው አጎራባች ክልሎች የሚሠጡትን እገዛ ያቀናጃል፡፡
፫. አግባብ ያላቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶችና ክልሎች የሚሳተፉበት ዓመታዊ ስብሰባ ይጠራል፤
፬. ቦርዱን በመወከል ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡፡

፱. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>
ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር
አዲስ አበባ

1) Serve as the main office of the Board and as a center that coordinates Federal support; follow-up the implementation of the decision of the Board;
2) Coordinate the support which is more capable to neighboring regions may provide;
3) Convene annual meeting in which the relevant ministries and the regions participate.
4) Represent the Board in its dealings with third parties.

9. *Effective Date*
This regulation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Meles Zenawi**
**Prime Minister of the Federal**
**Democratic Republic of Ethiopia**
**Addis Ababa**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE